በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1990 ዓ.ም. የጤናና አመጋገብ ጥናት የኤዲተሮችና ኮደሮች መመሪያ

አዲስ አበባ
ግንቦት 1990 ዓ.ም.

## የ1990 የጤናና የአመጋገብ ጥናት
## የተሞሉ መጠይቆች ኤዲትና ኮድ ማድረጊያ መመሪያ፡

### ሀ. ኤዲቲንግ፡

ከልዩ ልዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ኤዲት ማድረግ /ማረም/ የመረጃውን ጥራት ለመገምገምና እንደዚሁም ስህተቶችን፡ የሚቃረኑ መረጃዎችን፡ ሳይሞሉ የቀሩትን /omissions/ . . . ወዘተ በማረም የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል፡፡ ኤዲቲንግ ማለት የተሰበሰበውን መረጃ ሁኔታ በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው፡፡ ኤዲተሩ /አራሚው/ ይህንን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የመረጃ መሰብሰቢያው ፎርም /መጠይቅ/ ለመረጃ ሰብሳቢው በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ኤዲተሩ /አራሚው/ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

### 1. ሳይሞሉ የቀሩት መረጃዎች፡

በፎርሙ ሳይሞሉ የቀሩትን መረጃዎች በመፈለግ መመሪያውን በመከተል አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው፡፡ ሳይሞሉ በቀሩ መረጃዎች ፋንታ የሚሞላው መረጃ የሚገኘው ሌሎች የተሞሉ መረጃዎችን በማገናዘብና በመመርመር ነው፡፡ በተቻለ መጠን ለተዘለሉና ሳይሞሉ ለቀሩ መረጃዎች በሙሉ አስፈላጊው እርማት ተደርጎ መሙላት የሚያስፈልግ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ሆኖም ሳይሞሉ ለቀሩት መረጃዎች በፎርሙ ከታዩት መረጃዎች አመሰካክሮና መርምሮ ለማረም የማይቻል ከሆነ በፈጠራ መሙላት ስለማይገባ ሳያርሙ ዓምዱን ባዶውን መተው ያስፈልጋል፡፡ የዚህም ዓይነት ሁኔታ ኮድ ሲደረግ ላልታወቀ መልስ የሚሰጠው ኮድ ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡

### 2. ሊሆኑ የማይችሉና የማይመለሱ መልሶች፡

ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችና የማይመለሱ መልሶችን በእርማት ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች በመመሪያው ከተሰጠው ውጭ የተመለሱ መልሶች ሲሆኑ ለምሳሌ ባለፉት 14 ቀናት በሽታው ለስንት ቀን ቆየብዎት? ለሚለው ጥያቄ በዓምዱ የሰፈረው ቀናት ብዛት ከ14 ቀናት በላይ ከሆነ ይህ ሊሆን የማይችል መልስ በመሆኑ መታረም አለበት፡፡ የማይመስሉ መልሶችን በተመለከተ የጋብቻ ሁኔታን እንደምሳሌ ብንወስድ የአንድ ሰው የጋብቻ ሁኔታ፡

1/ ፈጽሞ ያላገባ/ያላገባች
2/ ያገባ/ያገባች
3/ ባል/ሚስት የሞተባት/የሞተችበት

4/ የተፋታ/የተፋታች

ሲሆን ይህም መረጃ የሚሞላው <u>እንደ ሁኔታው</u> ለቤተሰብ አባላት በሙሉ ነው:: ስለዚ ህ ለአንድ እድሜው ሶስት ዓመት ለሆነ ህጻን የጋብቻ ሁኔታ "ሚስት የሞተችበት" ተ ብሎ ቢሞላ በዚህ ዕድሜው አግብቶ ሚስቱ ልትሞትበት ስለማይችል መልስ ሊሆን የ ማይችል በመሆኑ መታረም አለበት::

3. <u>የሚቃረኑ መልሶች፣</u>

የሚቃረኑ መልሶችንም ማረም ተገቢ ነው:: የሚቃረኑ መልሶች የሚገኙት ከሁ ለት ወይም ከዚያ የበለጡ ሊዛመዱ የሚችሉ መልሶች ሳይዛመዱ ሲቀሩ ነው:: ለምሳሌ ባለፉት 14 ቀናት በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎታል? ተብሎ ተጠይቆ ኮድ «2 » የለም ለተመዘገበላቸው በሚቀጥለው ዓምድ የጉዳቱ ውጫዊ ምክንያት ተመዝግቦ ጉዳቱ ለ5 ቀናት ቆይቶባቸዋል እንዲሁም ለ1 ቀን የዘወትር ተግባራቸው አቋርጠዋል ተብሎ ከተሞላ በኋላ የእነዚህ ዓምዶች መልስ የሚቃረኑ መልሶች ናቸው::ይሄውም ጉ ዳት ላልደረሰበት ሰው የጉዳቱን ውጫዊ ምክንያትና ሌሎች ዓምዶች መጠየቅ አያስፈ ልግም:: ነገር ግን ለዓምድ 24 የተሞላው ኮድ ስህተት ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ እንደዘ ሁ ዓይነቱ እርስበርሳቸው የሚቃረኑ መልሶች ተመዝግበው ሲገኙ ከቀሩት ዓምዶች ጋ ር በማገናዘብ መረጃው መታረም ይኖርበታል::

4. <u>ጽሑፉን ለማንበብ የሚያስቸግሩ መልሶች፣</u>

በትክክልና በደንብ የማይነበቡ መልሶችን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል:: በ ተጨማሪም እርማቱ በሚደረግበት ወቅት የሚጻፉ ጽሑፎች ሁሉ በደንብና በቀላሉ የ ሚነበቡ መሆናቸው መገንዘብ ያስፈልጋል::

5. <u>ከመመሪያ ውጭ ስለተሞሉ</u>

በዚህ ጥናት ከመመሪያ ውጭ የተሞሉ መረጃዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ከፍተ ኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ:- የትምህርትና የጋብቻ ሁኔታ የሚጠየቀው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው:: ስለዚህ ዕድ ሜው 8 ዓመት ለሆነው ህፃን የትምህርት ሁኔታ ተሞልቶለት ቢገኝ ምንም እንኳ ዕድ ሜያቸው 7 ዓመት የሆናቸው ህፃናት በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ቢች ሉም መመሪያው ዕድሜያቸው 10 ዓመት እስካልሞላ ድረስ ስለትምህርት ሁኔታ የሚ ያመለክቱ መረጃዎች እንደማይጠበቅባቸው ስለሚገልጽ የተሞላው መረጃ ከመመሪያ ውጭ ስለሆነ መሠረዝ ይኖርበታል:: በተጨማሪ የዓምዶችን ቅደም ተከተል ለማመልከ ት መረጃዎች ሲሞሉ ከየትኛው ዓምድ ወደ የትኛው ማለፍ እንደሚገባ በመጠይቁ ላ ይ በግልጽ ተመልክቷል:: ስለሆነም መረጃዎች ይህንኑ ተከትለው መሞላት ስለሚገባቸ

ው በመጠይቁ ላይ በተመለከተው መሠረት ያልተሞሉ መረጃዎች ከተገኙ መታረም ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ በዓምድ 19 ኮድ «2» ከተሞላ ቀጣይ ዓምዶች ከዓምድ «20-23» በሠረዝ መታለፍ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ከዓምድ «20-23» ያሉት ዓምዶች ተሞልቶ ከተገኙ ዓምዶቹን በማገናዘብ ማስተካከልና ማረም ያስፈልጋል። በመጠይቁና በመመሪያው ውስጥ በግልጽ እንደተመለከተው ለአሠራር ያመች ዘንድ መረጃዎች በኮ ድ ብቻ (ከጥቂተ ዓምዶች በስተቀር) እንዲገለጽ ተደርጓል። ሆኖም አንዳንድ መረጃ ሰ ብሳቢዎች በስህተት መልሶቹን በቃላትና በኮድ ሊመዘግቡ ይችላሉ። ይህ አሠራር በተ ለይ መረጃዎች በኮምፒዩተር በሚቀነባበሩበት ወቅት ችግር ስለሚፈጥሩ በቃላት የተመ ዘገቡትን መረጃዎች በመሠረዝ በኮዶቻቸው ብቻ መግለጽ ያስፈልጋል።

ለ. <u>ኮዲንግ፡</u>

ኮዲንግ ማለት በፎርሙ የተሰጡትን መልሶች ወደ አሀዝ መለወጥ ነው። ይህም አሀዝ በቀላሉ መረጃውን በኮምፒውተር ለማቀነባበር ይረዳል። የእርማትና (Editing) የኮድ የማድረግ ተግባር በማጣመር ይካሄዳል። በዚህ ፎርም የተሞሉት መረጃዎች በ አብዛኛው አስቀድመው ኮድ ተደርገዋል። ለምሳሌ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ሃይ ማኖት . . . ወዘተ ናቸው። ለነዚህ መልሶች የእርማት ተግባር ለማከናወን ኮዶቹ በ መመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው። እንደ አዲስ ኮድ መደረግ ያለባቸው መልሶች ደግሞ በክፍል 1 የአካባቢ መለያ መልሶች ማለት ከአምድ 1-6 ያሉት 6 ዓምዶች ናቸው። እነዚህን መልሶች ኮድ ለማድረግ የሚረዱ የኮድ ዝርዝር ይሰጣል። የኤዲቲንግና የኮዲንግ መመሪያም የአሠራሩን ሁኔታና ዘዴ የሚገልጽ ጽሑ ፍ ነው።

## <u>የኤዲቲንግና የኮዲንግ አሠራር መመሪያ፡</u>

የኤዲቲንግና ኮዲንግ ተግባር በማከናወን ለሚደረገው እርማትና ቃላትን ወደ አሃዝ ለውጦ ለመጻፍ በደንብ የተቀረጸ በቀይ ወይም በሰማያዊ ከለር የሚጽፍ እርሳ ስ መጠቀም ያስፈልጋል። እርማቱ ሲደረግ ከዚህ በፊት የተጻፈውን በማጥፊያ ሳይጠ ፋ ሊነበብ በሚቻል ሁኔታ በመሠረዝ እርማቱን ከላይ መጻፍ ነው። ይህንን ተግባር ስ ከናወን በመመሪያው የአስተራረሙ ዘዴ መግለጫ ያልተሰጠበት ሁኔታ ሲያጋጥም ለ ሚደረገው እርማት /ስህተት፣ የማይመስል መልስ፣ ሳይሞላ የቀረ መረጃ፣ ሊነበብ የማ ይችል መልስ . . . . ወዘተ/ የሥራውን ተቆጣጣሪ ማማከር አስፈላጊ ነው።

## <u>የእያንዳንዱ ዓምድ ኤዲትና ኮድ አደራረግ መመሪያ፡</u>

ክፍል 1፡- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ለአንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ መጠይቆች ከተሞላለት በመጀመሪያው መጠይቅ በዓምድ 1-10 የተሞሉት የአካባቢ መለያ መረጃዎች ሁሉ ለቤተሰቡ በተሞሉት መጠይቆች ሁሉ እንዳሉ ተደግመው መጻፋቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

ዓምድ 1-7፡- በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ መጻፍ ያለባቸው ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ/ከፍተኛ ቀበሌ/ገ/ማህበር እና የቆጠራ ቦታ ስም ናቸው፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ እነኚህ ዓምዶች አንድም ሳይዘለል በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከነዚህ ዓምዶች አንዱ ሳይሞላ ቢቀር በሌሎች ዓምዶች ውስጥ ከተመዘገቡት መረጃዎች ጋር በማመሳከር መሞላት አለበት፡፡ ለምሳሌ በዓምድ 1 ውስጥ የክልል ስም እና በዓምድ 3 ውስጥ የወረዳ ስም ተመዝግቦ በዓምድ 2 ውስጥ የዞን ስም ባይሞላ የክልሉንና የወረዳውን ስም በማየት የዞን ስም ለይቶ መጻፍ ይቻላል፡፡ ከዚያም በነዚህ ዓምዶች ውስጥ የሰፈረ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ/ከፍተኛ፣ ቀበሌ/ ገ/ማህበር ስም ሁሉ የቦታዎችን ስም ኮድ ለማድረጊያ በተዘጋጀው የኮድ ዝርዝር ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም በኮድ ዝርዝሩ መሠረት በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ ኮድ ለማድረጊያ በተመደቡት ቦታዎች/ካርድ ኮለሞች/ ውስጥ ትክክለኞቹ ኮዶች ይሞሉላቸዋል፡፡

ዓምድ 8፡- የተመረጡ ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር፡- የሚለው የተሞላው ቁጥር ባለሁለት ዲጂት ሆኖ በትክክል መስፈሩንና ቁጥሩ በደንብ የሚነበብ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለጤናና አመጋገብ ጥናት የሚመረጡ ቤተሰቦች 25 ስለሆነ በዚህ ዓምድ የሚመዘገበው ከ25 መብለጥ የለበትም፡፡

ዓምድ 9፡- የቤተሰብ አባላት ብዛት

በዚህ ዓምድ ውስጥ የቤተሰብ አባላት ብዛት ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ዓምድ የተመዘገበው መረጃ ከዓምድ 12 /የመደበኛ ቤተሰብ አባላት/ ጋር የሚዛመድ በመሆኑ በሁለቱ ዓምዶች ላይ የሰፈረው የአባላት ብዛት ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡ ካልሆነ በኤዲቲንግ መስተካከል ይኖርበታል፡፡

ዓምድ 10፡- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም

በዚህ ዓምድ የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ዓምድ የተመዘገበው ስም በዓምድ 12 ከሰፈረው ስሞች መካከል ከአንዱ የአባላት ስም ጋር አንድ መሆን ይኖርበታል፡፡

## ክፍል 2፡- የቤተሰብ አባላት የዲሞግራፊ ባሕሪያት፣

ዓምድ 11፡- ተራ ቁጥር፡- በዚህ ዓምድ ከ01 እስከ 10 የቤተሰብ አባላት መመዝገብ የሚችል አስቀድሞ ተሞልቷል፡፡ በመጀመሪያው መጠይቅ ላይ 10 ሰዎች ከተመዘገቡ የቤተሰቡ አባላት የተመዘገቡበት ሌላ ተከታይ መጠይቅ መኖሩ ወይም አለመኖሩ መረጋገጥ አለበት፡፡ ከአንድ መጠይቅ በላይ ለቤተሰቡ መጠቀሙ ከታወቀ በሁለተኛው መጠይቅ ተራ ቁጥር 01 ሳይሆን ከ11 መጀመር አለበት፡፡ እንዲሁም ሌሎች ቀጣይ ተራ ቁጥሮች በ02 ፈንታ 12፣ በ03 ፈንታ 13፣ ... ወዘተ እያለ እስከ መጨረሻው መቀጠሉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻ ለተመዘገበ የቤተሰብ አባል የተሰጠው ተራ ቁጥር በጠቅላላ ከአሉት ከቤተሰቡ አባላት ብዛት ጋር እኩል መሆን አለበት፡፡

ዓምድ 12፡- መደበኛ የቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም፡-

ይህ ዓምድ ኮድ አይደረግም፡፡

ዓምዱ ሌሎች ዓምዶች በሚታረሙበትና ኮድ በሚሰጣቸው ጊዜ ለማመሳከር ይጠቅማል፡፡

ዓምድ 13፡- ፆታ፡- እዚህ ዓምድ ውስጥ የያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ፆታ በኮድ/1 ወይም 2 መሆኑ/ መገለጽ አለበት፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል "1" ወይም "2" የሚል መልስ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም "1" የሚለው መልስ ወንድ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ብቻ "2" የሚለው ኮድ ደግሞ ሴት ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ብቻ መመዝገቡን ቀጥሎ በተጠቀሱት ዘዴዎች ማረጋገጥና ካስፈለገም ማረም ነው፡፡

እነዚህም የሚረጋገጡት በዓምድ 12 ውስጥ ከሠፈረው ስማቸው፣ ዕድሜአቸው ከ15 ዓመት በላይ ለሆኑ ሴቶች በዓምድ 41-46 ስለ ወሊድ ተጠይቀው እንደሆነ በማመሳከር እና በማዛመድ ነው፡፡ በተጨማሪም በዓምድ 20 እና 21 ከሠፈሩት በሽታዎች መካከል አንዳንዶቹ ከሴቶች ላይ ብቻ የሚታዩ ስለሆነ አንዳንድ አባላት ሴት ስለመሆናቸው ተጨማሪ ማረጋገጫ

ሊሆኑ ይችላሉ ለምሳሌ ውስብስብ እርግዝና፣ ውርጃ፣ አስቸጋሪ ወሊድ ፣ ... የሴቶች የጤና መታወክ ናቸው።

አልፎ አልፎ ምናልባት የእያንዳንዱ ሰዎች ጾታ ካልተሞላ ከላይ በተዘረዘሩት ዓምዶች ውስጥ የተሠጡትን መልሶች በማገናዘብ ጾታውን ማወቅ ስለሚቻል ትክክለኛውን ኮድ መጻፍ ነው።

ዓምድ 14:- ዕድሜ በሙሉ ዓመት:-

የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ በካርድ ኮለም 26 እና 27 ውስጥ በሙሉ ዓመት ብቻ መመዝገብ አለበት። የዕድሜ አመዘጋገብ ዓመት ከ"00" እስከ "97"

፣ የተመዘገበ ነው። ስለሆነም ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ አባላት ዓመት 01፣ 02፣ 03፣ 04፣ 05፣ 06፣ 07፣ 08፣ እና 09 ሲመዘገብላቸው ዕድሜያቸው 98 እና በላይ ለሆኑት አባላት ግን "97" ብቻ ተብሎ መፃፍ አለበት። ዕድሜው ከ97 ዓመት በታች ለሆነ ሌላ ዕድሜ ላለው አባል ግን ያው ዕድሜው እንዳለ በሙሉ ዓመት ይጻፍለታል። በተጨማሪም በአጠቃላይ የማንኛውም አባል ዕድሜ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሌሎች አባለት/ ወላጆች፣ ልጆች፣ . . . .ወዘተ/ ከተመዘገቡት ዕድሜዎች ጋር ማመሳከር ያስፈልጋል። በተለይ ዕድሜያቸው ያልተመዘገበ አባለት ሲያጋጥም በዚህ ዘዴ ዕድሜያቸው ያልተመዘገበ አባላት ሲያጋጥም በዚህ ዘዴ ዕድሜያቸውን ገምቶ ለመመዝገብ መሞከር ያስፈልጋል። ዕድሜው በምንም ዓይነት ሊታወቅ ላልቻለ አባል ግን "99" ይጻፋል።

ዓምድ 15:- ሃይማኖት:-

እዚህ ዓምድ ውስጥ የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ሃይማኖት በኮድ ከዚህ በታች በተገለፀው መሠረት መገለጽ አለበት።

1= ኦርቶዶክስ
2= ፕሮቴስታንት(ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት፣ መካነየሱስ፣ ሙሉወንጌል፣ መሠረተ ክርስቶስ ፣...ወዘተ)
3= ካቶሊክ
4= እስላም (ሙስሊም)
5= ባህላዊ
6= ሌላ /ለምሣሌ:- ሂንዱ፣ ጆሆባ፣ ኤቲስት፣ ...ወዘተ/

ስለዚህ መጀመሪያ ዓምዱ ውስጥ የሠፈሩት መልሶች ሁሉ በኮድ የተገለ ጹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ምናልባት በፊደላት የተጻፈ መልስ ቢ ገኝ ተሠርዞ በኮድ መተካት አለበት። እዚህ ላይ የአንድ ቤተሰብ አባላት በሙ ሉ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ዓይነት ሃይማኖት እንዲኖራቸው ቢገመትም አንዳን ድ ጊዜ የተለያዩ አባለት የተለያዩ ሃይማኖቶች ሊኖራቸው ስለሚችል የያንዳን ዱ አባል ሃይማኖት ሳልተገለጸ ጨቅላ ሕፃን ቢኖር የአባቱ ሃይማኖት ይሰጠዋል ።

<u>ዓምድ 16</u>:- <u>ብሔረሰብ</u>:- በዓምዱ የያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ብሔረሰብ በካርድ ኮለም 29 እና 30 ኮድ ተሞልቷል። ቀደም ሲል ለሃይማኖት እንደተገለጸው የቤተሰበ - አባላት ብሔረሰብ አንድ አይነት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። በዚህ መሠረት ቀጥሎ በተዘረዘሩት የብሔረሰብ ኮዶች አማካኝነት ለተገለፀው ብሔረሰብ ትክ ክለኛ ኮድ መሰጠቱን ማረጋገጥ ነው። ብሔረሰባቸው ተጽፎ ኮድ ካልገባላቸው በፊደል የተጻፈውን ሰርዞ ትክክለኛ ኮድ ተመርጦ ይገባላቸዋል።

ከዚህ በታች በተሠጠው የብሔረሰቦች ዝርዝር ውስጥ ያለተጠቀሰ ብሔ ረሰብ ስም ተሞልቶ ቢገኝ ካስፈለገ ተቆጣጣሪውን በማማከር የአጻጻፍ ስሕተት ወይም ልዩነት እንዳይሆን በመመርመር እውነት በዝርዝሩ ውስጥ የሌለ መሆ ኑን ካረጋገጡ በኋላ ኮድ “98”

መጻፍ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የአንድ ቤተሰብ አባላት በሙሉ የአንድ ብሔረ ሰብ አባላት እንደሚሆኑ የሚጠበቅ ቢሆንም አልፎ አልፎ በአንድ ቤተሰብ ው ስጥ የተለያዩ ብሔረሰቦች አባላት የሆኑ ግለሰቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ምናልባት ብሔረሰቡ ያለተገለጸ ጨቅላ ሕፃን ቢገኝ የአባቱ ብሔ ረሰብ ይሰጠዋል። የብሔረሰብ ስም ዝርዝርና ኮድ ከዚህ በታች ቀጥሎ ቀርቧል ።

ዓምድ 17፡- ማንበብና መጻፍ ከቻሉ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ካልቻሉ «00» ይመዘገባል

ዕድሜአቸው 10 ዓመት ወይም በላይ ለሆኑ ሁሉ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ወይም የማይችሉ መሆናቸው ተጠይቆ ለማይችሉ «00» ሲመዘገብ ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ግን የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች መ ሠረት ይመዘገባል። ምናልባት መልሱ በፊደላት ተጽፎ ቢገኝ ስርዞ በምትኩ ት ክክለኛውን ኮድ መጻፍ ነው። ኮዶቹም የሚከተሉት ናቸው።

00= ማንበብና መጻፍ የማይችል

01= የአንደኛ ክፍል ትምህርትን ሳጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ

02= የ2ኛ ክፍል ትምህርትን ሳጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ፣

03= የ3ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ

04= የ4ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

05= የ5ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

06= የ6ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

07= የ7ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

08= የ8ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

09= የ9ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

10= የ10ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

11= የ11ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

12= የ12ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

20 ሰርተፊኬት በትምህርት መስጫ ከታወቁ ተቋሞች (ኮሌጆች፣ ዩኒቨርስቲዎች ወይ ም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ወይምዲግሪ ለ ማስገኘት ባልታቀደ ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይትምህ ርት ለፈጸሙ ሁሉ፣ ፕሮግራሙን አጠናቀው ሰርተፊኬት የተቀበሉ ሁሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ።

21 ዲፕሎም ያልጨረሱ

ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ በከፍተኛ ትም ህርት መስጫ ከታወቁ ተቋም ወይም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስ ቲ ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ለ ማስገኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከ ዚያ በላይ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲፕሎም ሳላገኙ ሁሉ።

22 ዲግሪ ያልጨረሱ

ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ፣ቢ.ኤስ.ሲ) ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕ ሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርስቲ የአንድ ዓመት ወይም የበ ለጠ ትምህርት ሳጠናቀቁ ግን ዲግሪ ሳላገኙ ሁሉ።

23ዲፕሎም
በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋም (ኮሌጅ) ዩኒቨርስቲ ወይም ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሁሉ።

24 ዲግሪና በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪ ላገኙ፣

95 መሠረተ ትምህርት
በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ማንበብና መፃፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ላልቀጠሉ ሁሉ፤

96 መደበኛ ያልሆኑ
የቄስ የቁርዓንና የመሳሰሉት ትምህርት ቤቶች በመማር ማንበብና መፃፍ የሚችሉ (ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትም ህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጎም የማይቻል)። እንደዚሁም በራ ሳቸው ጥረት የግለሰቦችን ዕርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የ ቻሉ እዚህ ይመደባሉ። በተጨማሪም በመደበኛ ት/ቤት አንደኛ ክፍል ያላጠናቀቁ ሆነው ነገር ግን ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በዚህ ክፍል ይካተታሉ።

<u>ዓምድ 18</u>:- <u>የጋብቻ ሁኔታ</u>:- ለእያንዳንዱ ዕድሜው 10 ዓመት ወይም በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል የጋብቻ ሁኔታ ከዚህ በታች በተመለከተው የኮድ አሠጣጥ መሠረት እዚህ ዓምድ ውስጥ በኮድ መስፈር አለበት።

1= አግብተው የማያውቁ
2= በትዳር ላይ ያሉ
3= የተፋቱ
4= የሞተባቸው

ስለዚህ መጀመሪያ በዓምዱ ውስጥ 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ የሚል መልስ የተጻፈ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪም ከዕድሜ ጋር በማገናዘብ ማረም ያስፈልጋል። ዕድሜው 10 ዓመት ለሆነ ልጅ "2" የሚል መልስ ገብ ቶ ቢገኝ ትክክል መሆኑ በጣም ያጠራጥራል።

<u>ዓምድ 19-23</u>:- <u>ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ስለደረሱ በሽታዎች</u>:- እነዚ ህን ዓምዶች ውስጥ የሚሰጡ መልሶች እርስ ሰርሳቸው መመካከር አለባቸው። ለምሳሌ ዓምድ 20 ወይም 21 ውስጥ የበሽታ ስም ከተፃፈ በዓምድ 19 ውስጥ «1» የሚል መልስ መግባት አለበት። ወይም ለዓምድ 20 እና 21 ውስጥ የ

በሽታ ስም ካልተመዘገበ በዓምድ 22 እና 23 ውስጥ የሚጻፍ የቀናት ብዛት
አይኖርም፡፡

<u>ዓምድ 19</u>፡-<u> በሽታ ደርሶብዎት ነበር?</u>

እዚህ ዓምድ ውስጥ የሚሞላው መልስ «1» ወይም «2» መሆን ብቻ አለበት
እንጂ ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ይህንን ማጣራት ያ
ስፈልጋል፡፡ ከዚያም በዓምድ 20-24 ውስጥ ከተሞላው ጋር የሚገናዘብ መሆኑ
ን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በዓምድ 20 እና 21 ውስጥ የበሽታ ስም ተጽፎ በ
ዓምድ 19 ውስጥ ከ«1» የተለየ ነገር ከተጻፈ የተመዘገበውን አጥፍቶ «1» ማ
ድረግ ያስፈልጋል፡፡

<u>ዓምድ 20 እና 21</u>፡- <u>ለዓምድ 19 መልሱ “1" ከሆነ በሽታው ምን ነበር ወይም</u>
<u>በሽታዎቹ ምን ምን ነበሩ?</u>

በተባለው ጊዜ በበሽታ ምክንያት ታሞ ለነበረ ማንኛውም ሰው የአንድ ወይም
ቢበዛ የሁለት በሽታዎች ስም ሊመዘገብለት ይችላል፡፡ ሁለት በሽታዎች ከነበሩ
ት የአንደኛው እና ከባዱ ህመም ስም በዓምድ 20 ውስጥ መጻፍ ሲሆን የሁለ
ተኛው ከባድ በሽታ ስም ደግሞ በዓምድ 21 ውስጥ ይመዘባል፣ አንድ በሽታ
ብቻ ከደረሰበት ግን የበሽታው ስም በዓምድ 20 ውስጥ ብቻ መጻፍ አለበት፡፡
ስለዚህ አነኚህ ዓምዶች በእንደዚህ ሁኔታ መሞላታቸውን ካስፈለገም እርማት
በማድረግ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ቀጥሎም የበሽታ ስምና ኮድ ሲመዘገብ መስ
መር በማሳሳት ስሕተት እንዳይኖር መረጋገጥ አለበት፡፡ ለምሳሌ የነፍሰ ጡር ሴ
ት በሽታ/ ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ሴቶች በሽታ ወንድ ወይም ሕፃን ለሆነ የ
ቤተሰቡ አባል ስም አኒያ ከተጻፈ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ መስመር ዝቅ
ወይም ከፍ ብሎ የነፍሰ ጡር፣ አራስ ወይም ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ሴት ስ
ም ካለ ይህ በሽታ እስዋን የሚመለከት መሆን ስላለበት ሁኔታውን ከዕድሜዋ፣
የመጨረሻ ልጅዋ ዕድሜና ካስፈለገም የነፍሰ ጡርነትና ሁኔታ ከተሞላ የአመ
ጋገብ መጠይቅ ጋር በማገናዘብ የበሽታው ስምና ኮድ በስምዋ አኳያ መጻፍ
አለበት፡፡ እንደዚሁም አብዛኛውን በአዋቂ ላይ የሚታይ በሽታ ለሕፃን /ከ5 ዓ
መት በታች/ ወይም አብዛኛውን ጊዜ በሕጻን ላይ የሚታይ በሽታ ለአዋቂ ተ
ጽፎ ከተገኘ በተመሳሳይ መልክ ለማስተካከል መሞከር ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪ
ም በመጠይቁ ውስጥ ተሞልቶ መምጣት ያለበት የበሽታ ስምና ኮድ መሆን ሲ
ኖርበት የበሽታው ምልክቶች (Syptoms) ተጽፎ ቢገኝ ቀጥሎ ከተመለከተው የ
በሽታዎች ስሞችና ምልክቶቻቸው ዝርዝር ጋር በማገናዘብ በሽታውን በትክክ
ል ለይቶ የተጻፉትን ምልክቶች አጥፍቶ ስሙን እና ኮዱን ብቻ መጻፍ ያስፈል
ጋል፡፡

## ት ኩ ሳ ት

11 እያቋረጠ የሚመለስ ከፍተኛ ትኩሳት ከማንቀጥቀጥ ብርድ ብርድ ማለት ጋርና የሰውነት ድካም፡ ___________________________ "<u>ወባ</u>"

12 ትኩሳትና ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሰውነት የሚጠፉ ሽፍታ ጋር፡ ___"<u>ኩፍኝ</u>"

13 ትኩሳት ከማቅለሽለሽና ዓይን ብጫ መሆን ጋር ቀለሙ የነጣ ሰገራ፡ መገጣጠሚያ ላይ ቁርጥማት ትውከት፡ ምግብ ማስጠላት፡ _________ "<u>የወፍ በሽታ</u>"

14 ትኩሳት ከአንገት መገተር ጋር፡ ትውከት እንዲሁም በሰውነት ላይ የሽፍታ ምልክት፡ ______________________________ "አንገት ገትር"

15 ትኩሳት ከከባድ ራስ ምታት ጋር አንዳንድ ጊዜ ሰውነት መሳት፡ ድካም፡ /ብዙውን ጊዜ በወረርሽኝ መልክ የሚዛመት/፡ __________ "<u>ተስቦ</u>" "<u>ሌላ ትኩሳት</u>"16 ሌላ ከላይ ያልተገለጹ የትኩሳት በሽታዎች፡ ለምሣሌ ጉድፍ ...ወዘተ

### ሳ ል

21 ለረጅም ጊዜ /3 ወር ወይም በላይ/ የቆየ ሳል ከወፍራም አክታ/ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል/ ከሰውነት ክብደት መቀነስ ጋር አንዳንድ ጊዜ መጠነኛ ትኩሳትና ሌሊት ማላብ፡ ____________________ "<u>ሳምባ ነቀርሳ</u>"

22 ለአጭር ጊዜ የቆየ /ከ3ወር ያነሰ/ ሳል፡ ትኩሳትና በደረት ዙሪያ ውጋትና ትንፋሽ ማጠር ጋር አክታ፡ ____________________ "<u>ኒሞኒያ</u>"

23 ኃይለኛ /አጣዳፊ/ሳል ከትኩሳትና ትክትክ ጋር ብዙውን ጊዜ ከ5 ዓመት በታች በሆኑ ልጆች የሚታይ፡ ____________________ "<u>ትክትክ</u>"

24 ሌላ ከላይ ያልተገለጹ የሳል በሽታዎችና ስሜቶች ለምሳሌ ጉንፋን፣ ትንፋሽ ማጠር፣ አዝማ፣ ውጋት ...ወዘተ ________________ "<u>ሌላ ሳል</u>"

<u>ተቅማጥና የሆድ በሽታ</u>

31

የሚያጣድፍ ቀጭን ዓይነ ምድር፣ ደም የተቀላቀለበት ሊሆን ይችላል አንዳንድ ጊዜም ንፍጥ የሚመስል እዳሪ ...ወዘተ በየቀኑ ከተለመደው ሁኔታ ይበልጥ በመደጋገም ሲከሰት ነው። ___________________ "<u>ተቅማጥ</u>"

32 በቀን ከ3 ጊዜ የበለጠ ተቅማጥ ከትውከት ጋር ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት፣___________________ "<u>ጋስተሮ ኢንቶራይቶስ</u>"

33 እንደ ወስፋት፣ ኮሶ የመሳሰሉት በበሽተኛው የታዩ የሆድ ትላትሎች፣ _____________________ "<u>ጥገኛ የሆድ ትላትል</u>"

34 ሌላ ተቅማጥና የሆድ በሽታ ምሳሌ የጨጓራ በሽታ፣ ሆድ መንፋት ...ወዘተ ______________________ "<u>ሌላ ተቅማጥና የሆድ በሽታ</u>"

<u>አንገትና እራስ ላይ የሚታዩ በሽታዎች</u>

41 በአንገት ላይ ከፊት በኩል በውጭ የሚታይ ስቃይ የሌለበት/የማያም/ እብጠት በተለይም ምራቅ፣ ውሃ፣ ምግብ ሲውጡ ወደ ላይና ታች የሚነቃነቅ፣ ____________________ "<u>እንቅርት</u>"

42 አንዳንድ ጊዜ መግል ያለው የጆሮ መታመም /የቆየ ያለመስማት፣ ችግርን አይጨምርም፣/ __________________________ "<u>የጆሮ ሕመም</u>"

43 የዓይን ሕመም ከዓይን አር ጋር ሊሆን ይችላል፣ /የአንድ ወይም የሁለት ዓይኖች መታወርን አይጨምርም፣_____________________ "<u>የዓይን ሕመም</u>"

44 በህጻናት ላይ የሚገኝ የጉሮሮ ህመም አንዳንድ ጊዜ በአንገት አካባቢ ከፊት በኩል ከውጭ /ከፍ ብሎ/ የሚታይ ሕመም ያለበት እብጠት፣ የመዋጥ ችግር ትውከት፣ ትኩሳት፣ "የጉሮሮ ሕመም"

45 የጥርስና የድድ ሕመም፣ ____________________ "የጥርስና የድድ ሕመም"

46 ሌላ የአንገትና የራስ በሽታ ምሳሌ ራስ ምታት፣ ነስር፣ ጆሮ ደግፍ ...ወዘተ ____________________ "ሌላ የአንገትና የራስ በሽታ"

## የአባለዘር በሽታ

51 በሴቶች ወይም በወንዶች ላይ የሚታይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚመጡ በሽታዎች ምሳሌ ጨብጥ፣ ቂጥኝ፣ በብልት ላይ ወይም አካባቢ ቁስል፣ እብጠት....ወዘተ____________________ "የአባለ ዘር በሽታ"

## በቆዳ ላይ የሚታይ በሽታ

61 አደጋ ሳይደርስ በቆዳ ላይ የሚታዩ ቁስሎች እከክ፣ ችፌ፣ ቁስል.... ወዘተ. ____________________ "በቆዳ ላይ ቁስል"

62 "የሰጋ ደዌ" ____________________ "የስጋ ደዌ"

63 በአንድ እግር ወይም በሁለት እግሮች ወይም በብልት ፍሬዎች ላይ የቆየ በጣም ትልቅ ዕብጠት____________________ "ዝሆኔ"

64 ሌላ በቆዳ ላይ የሚታዩ በሽታዎችና ስሜቶች ለምሳሌ ለምጥ፣ አባ ሰንጋ፣ ....ወዘተ.____________________ "ሌላ የቆዳ ላይ በሽታ"

## በተለይ ነፍስ ጡሮችን፣ አራሶችንና ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ሴቶችን ሁሉ የሚመለከቱ የጤና ችግሮች፣

71 የጤና መታወክ ያለበት እርግዝና/ለምሳሌ ከማህፀን ወይም ከብልት ደም መውጣት፣ እግር ማበጥ፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ መገርጣት፣ ...ወዘተ. ____________________ "ውስብስብ እርግዝና"

72 ከሰባት ወር ዕርግዝና በፊት የሆነ ውርጃ፡______________ "ውርጃ"

73

በወሊድ ጊዜ የጤና ችግር ለምሳሌ በወሊድ ጊዜ ከመጠን በላይ ደም መፍሰስ፡ ረጅም ጊዜ የወሰደ አድካሚ ምጥ፡__________ "አስቸጋሪ ወሊድ"

74 ከወሊድ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ በወሊድ ምክንያት የጤና ችግር ለምሳሌ ትኩሳት__________________ "የአራስ የጤና ችግር"

75 "የወር አበባ በሽታና ሌሎች የእናቶች በሽታዎች"______________ "የወር አበባ በሽታና ሌሎች የእናቶች በሽታዎች"

ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ በሽታዎች

81 የሰውነት መክሳት ከኃይል ማጣት ጋር የሰውነት ማበጥ፥ በደም ማነስ መገርጣት፥ የራስ ጠጉር ቀለም መለወጥ በተለይ የሕፃናት በሽታ፥____________ "የተጓደለ አመጋገብ"

82 የመንጋጋ አልከፈት ማለት ከጡንቻዎች ጋር ቁስል የነበረው ወይም ያለው ወይም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተወለደ/ከወር ወዲህ/ወይም በቅርብ ጊዜ የወለደች/ከወር ወዲህ/________________ "መንጋጋ ቆልፍ"

83 የአእምሮ በሽታ ለምሳሌ እብደት፥______________ "እብደት"

84 ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ የጤና በሽታዎች ለምሳሌ አጠቃላይ ድካም፥ ልብ ድካም፥ ቁርጥማት፥ የኩላሊት በሽታ፥ የደም ብዛት፥ የደም ማነስ፥ የስኳር በሽታ...... ወዘተ______________ "ሌሎች ከላይ ያልተጠቀሱ በሽታዎች"

ኮድ፡ 99 = «ያልተገለፀ» = ለዓምድ 19 መልሱ 1 በመሆኑ በዓምድ 22 ውስጥ የቀናት ብዛት በመጻፉ ሰውዬው በወቅቱ በሽታ እንደደረሰበት ግልጽ ሆኖ እያለ የበሽታ ስም በዓምድ 20 እና 21 ሳይኖር ሲቀር ወይም የተጻፈው የበሽታ ስም ከላይ በተሰጠው ዝርዝር መሠረት ሊተረጎም የማይችል ሲሆን።

ዓምድ 22:- በዓምድ 20 እና 21 የተጠቀሰው ሕመም በጠቅላላ ለስንት ቀናት ቆየበት?

በዓምድ 20 እና 21 ሕመም እንደደረሰበት ለተመለከተለት የቤተሰቡ አባል ሕመሙ በጠቅላላው ለስንት ቀናት እንደቆየበት በዚህ ዓምድ ውስጥ ይጻፋል:: በ ዓምዱ የሚጻፈውም የቀናት ብዛት ከ "01" እስከ "14" ሊደርስ ይችላል እንጂ በምንም ዓይነት "00" ወይም "_____" ሊሆን አይችልም:: ምናልባት የሕመሙ ስም በዓምድ 20 ተጽፎ የታመሙበት ቀናት ግን ባይጻፍ ሁኔታው ያልተገለጸ ስለሆነ "99" መጻፍ አለበት::

ዓምድ 23- በሕመሙ /በሕመሞቹ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ?

በዓምድ 20 እና 21 ሕመም እንደደረሰበት ለተመለከተለት ማንኛውም ሰው በሕመሙ/በሕመሞቹ ምክንያት ጥናቱ በሚመለከተው 14 ቀን ውስጥ የዘወትር ተግባሩን ያላከናወነባቸው ቀናት ብዛት ይጻፋል:: የቀናቱ ብዛት ከ14 ሊበልጥ ስለማይችል ከ14 የበለጠ ቀናት ብዛት ተጽፎ ቢገኝ ሰርዞ 14 ማድረግ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ከ10 ያነሰ የቀናት ቁጥር ሲጻፍ በስተግራው "0" በማስቀደም ባለ ሁለት ዲጂት አድርጎ መጻፍ ስለአለበት ይህም በትክክል መሠራቱን ማረጋገጥና ካስፈለገም ማስተካከል ነው:: እንደዚሁም አንድ በሽታ የደረሰበት ግለሰብ ከዘወትር ተግባሩ ላይተጓጎል ስለሚችል በዚህ ዓምድ ውስጥ "00" ሊገባ መቻሉን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ነገር ግን በሽታ ደርሶበት በዚህ ዓምድ ውስጥ ምንም ሳይገለጽ ቢገኝ ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር "00" ወይም ሌላ ተስማሚ ቀን ወይም "99" ይገባለታል::

ዓምድ 24-27 በአደጋዎች ምክንያት ባለፉት 14 ቀናት ስለደረሱ ጉዳቶች፤

በእነዚህ አራት ዓምዶች ውስጥ የተሞሉ መልሶች እርስ በርሳቸው መመሳከር ስላለባቸው ኤዲት ሲደረጉ የሚመሳከሩ ወይም የሚስማሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ መሆን ይኖርበታል::

ዓምድ 24 :- በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል?

እዚህ ዓምድ ውስጥ ለማንኛውም የቤተሰብ አባል መጻፍ ያለበት ኮድ "1" ወይም ኮድ "2" ነው:: ከዚህ የተለየ ሊሆን ስለማይችል መጀመሪያ ይህንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: "1" ወይም "2" ያልተጻፈለት ግለሰብ ካለ እሚቀጥለው ዓምድ ውስጥ ለዚህ ግለሰብ የተጻፈው

ን መመልከት ያስፈልጋል። ይኸውም ዓምድ 25 ውስጥ “1”
ለተጻፈላቸው ሁሉ በዓምድ 28 እና 27 የቀናት ብዛት ስለሚሞላላቸው ግለሰ
ቡ የቀናት ብዛት ከተሞላለት ዓምድ 25 ውስጥ “1”
ይጻፍለታል። የቀናት ብዛት ካልተሞላ ግን “2” ይጻፍለታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ዓምድ 25 ውስጥ “1” ተሞልቶ ዓምድ “26 እና 27” ውስጥ የቀናት ብዛት ባይጻፍ ወይም ዓምድ 25 ውስጥ “2” ተሞልቶ ዓምድ 26 እና 27 ውስጥ የተሞላ የቀናት ብዛት ቢኖር መረጃ ሰብሳቢው ከሶስት አንድ ዓምድ ውስጥ መስመር ስቶ ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ በመጻፍ ሊሆን ስለሚችል በደንብ በማገናዘብ ሁኔታውን ለማስተካከል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

ዓምድ 25፡- ጉዳት ከነበረብዎት ጉዳቱን ያደረሰው ውጫዊ ምክንያት?

እዚህ ዓምድ ውስጥ ጉዳት ያደረሰው ውጫዊ ምክንያት የሚያሳይ ኮድ ተሞልቶ መገኘት ያለበት በዓምድ 25 ውስጥ የተጻፈው መልስ “1” ሲሆንና በዓምድ 26 እና 27 ውስጥ የቀናት ብዛት ተጽፎ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ቀጥሎም መልስ ሆነው የሰፈሩት ኮዶች እያንዳንዳቸው በትክክል ባለ ሁለት ዲጂት መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ኮዶቹም 01፣ 02፣ 03፣ 04፣ . . . ፣ 13 እና 14 ብቻ ናቸው። በመጨረሻም በዓምድ 24 ውስጥ ያለው መልስ “1” ሆኖ፣ በዓምድ 27 እና 26 ውስጥ የቀናት ብዛት ተሞልቶ በዚህ ዓምድ /በዓምድ 24/ ውስጥ የተሞላ ኮድ ከሌለና በመጠይቁ ውስጥ የተሞሉቱን መረጃዎች በማገናዘብና በማስተካከል ለመሙላት ካልተቻለ ሁኔታው ያልተገለጸ ስለሆነ “99” መጻፍ አለበት። ኮዶቹም ቀጥሎ ተመልክቷል።

01 = ሳይታሰብ በመውደቅ በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

02 = ከጋማ ከብት በመውደቅ ወይም በሌሎች ከብቶች በመረገጥ ወይም በመወጋት በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

03 = ሳይታሰብ በመቀጠል በደረሰ አደጋ ምክንያት /ለምሳሌ በእሳት፣ በፈላ ውሃ፣ በአሲድና በመሳሰሉት መቀጠል/፣

04 = በጦር መሳሪያ በደረሰ ያልታሰብ አደጋ ምክንያት/በጠብ ወይም በተንኮል ምክንያት የሆነውን አይጨምርም፣

05 = ሳይታሰብ መርዝ ወይም መርዝ ያለው ነገር በመውሰድ በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

06 = በተሽከርካሪዎች /ለምሳሌ በመኪና፣ በዶቅዶቄ፣ በባቡር...ወዘተ መጋጨት፣ መቀረት፣ መገልበጥ/በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

07 = ከሰው ጋር በመጣላት ወይም በልዩ ልዩ ምክንያቶች በሰዎች አማካኝነት በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

08 = በመነከስና በመነደፍ በደረሰ አደጋ ምክንያት /ለምሳሌ በውሻ፣ በአውሬ፣ በጊንጥ፣ በእባብ ....ወዘት/

09 = ራስን ለመግደል በመሞከር በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

10 = በምንጣሮ ጊዜ ሳይታሰብ በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

11 = በሚሰሩበት የቤት፣ የእርሻ ወይም የማምረቻ መሣሪያ (ለምሳሌ ሙቀጫ፣ ቢላዋ፣ መዶሻ፣ ማጭድ፣ ...ወዘተ) በደረሰ የመቆረጥ፣ የመወጋት፣ የመሰበር ...ወዘተ አደጋ ምክንያት)

12 = በጎርፍ ወይም በውሃ ሙላት በደረሰ ያልታሰበ አደጋ ምክንያት፣

13 = በእግር ላይ ወይም በሌላ የሰውነት አካል ላይ ዕቃ ወድቆበት በደረሰ አደጋ ምክንያት፣

14 = በሌላ ከዚህ በላይ ባልተጠቀሱ አደጋዎች ምክንያት፣

99 = ያልተገለጸ

<u>ዓምድ 26:- ጉዳት ከነበረብዎት ጉዳቱ በጠቅላላው ለስንት ቀናት ቆየብዎት?</u>

ይህ ዓምድ ኤዲት የሚደረገው ከሌሎች ዓምዶች በተለይ በዓምድ 24 እና 25 ውስጥ ከተሞሉት መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ልክ ዓምድ 25 ኤዲት በተደረገ በት መልክ ይሆናል። ሆኖም በተጨማሪ ሁለት ነጥቦችን ማስተዋል ያስፈልጋል፡ ፡ አንደኛ በዚህ ዓምድ ውስጥ መሞላት ያለበት የቀናት ብዛት በዓምድ 27 ው ስጥ ከተሞላው ሊበልጥ ወይም እኩል ሊሆን ይችላል እንጂ በምንም ዓይነት ሊ ያንስ ስለማይችል አንሶ ቢገኝ ሰርዞ እኩል ማድረግ ያስፈልጋል። ሁለተኛው በ ዚህ ዓምድ ውስጥ የሚጻፈው የቀናት ብዛት ከ14 ሊበልጥ አይችልም። /የሚገ ባው የቀናት ብዛት ከ"01" እስከ "14" ሊሆን ይችላል።/

<u>ዓምድ 27:- ጉዳት ከነበረብዎት በጉዳቱ ምክንያት የዘወትር ተግባርዎን ለስንት ቀናት አቋረጡ?</u>

በዓምድ 24 ውስጥ ያለው መልስ "1" ከሆነ ዓምድ 26 ውስጥ የቀናት ብዛት የግድ መፃፍ አለበት፡ የተሞላው የቀናት ብዛትም በምንም ዓይነት ከ14 መብለ ጥ ስለሌለበት በልጦ ቢገኝ ሰርዞ 14 ማድረግ ያስፈልጋል:: በዓምድ 24 ውስጥ መልሱ ሆኖ በዓምድ 26 የተሞላ የቀናት ብዛት ባይኖር በዓምድ 24 እና በሌ ሎች ዓምዶች ውስጥ የተሰጡት መልሶች ጋር በማገናዘብ ለማረም ካልተቻለ የ ቀናት ብዛት ያልተገለጸ ስለሆነ "99" መጻፍ ነው::

ዓምድ 28:- <u>ባለፉት 12 ወራት በበሽታ/በአደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶብዎታል?</u>

ይህ ዓምድ ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ባለፉት 12 ወራት በበሽታ/በአደጋ ምክ ንያት ጉዳት ደርሶባቸው ወይም አልደረሰባቸው እንደሆነ ተጠይቆ የሚሞላበት ዓምድ ነው:: ይህ ዓምድ ኤዲት በሚደረግበት ወቅት በዓምድ 24-27 ከተሞ ላው መረጃ ጋር ማገናዘቡ በጣም ጠቃሚ ነው:: ይሄውም ባለፉት 14 ቀናት በቤተሰቡ አባላት ላይ ጉዳት ደርሶበታል ተብሎ ሌሎች ቀጣይ ዓምዶች ከተሞ ሉ ለዓምድ 28 መልሱ የለም /ኮድ «2»/ ሳይሆን ኮድ «1» ይሆናል ማለት ነው:: ነገር ግን በዓምድ 28 የተሞላውን መረጃ መሠረት በማድረግ ዓምድ 24 ን ለማስተካከል መሞከር ስህተት ላይ ሊጥል ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረ ግ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ባለፉት 12 ወራት በአንድ አባል ላይ ጉዳት ደር ሶበታል ማለት የግድ ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ነው ጉዳቱ ያጋጠመው ማለት ስለማይችል ነው:: ባለፉት 12 ወራት ጉዳት ያጋጠመው ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ሊሆኑ ወይም ላይሆንም ይችላል:: ከዚህም በተጨማሪ ከዓምድ 30-38 ካለው ጋር ማገናዘብ እና ለመልሱ የተሰጡ ኮዶች «1» ወይም «2» ብቻ መ ሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 29:- <u>የሕክምና እርዳታ አገኙ /ባለፉት 12 ወራት/?</u>

ይህ ዓምድ ለሁሉም የቤተሰብ አባሎች ባለፉት 12 ወራት ታመው ወይም በአ ደጋ ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ለመፈወስ የሕክምና እርዳታ ማግኘት አለማ ግኘታቸው የሚገለጽበት ነው በመሆኑም በመጀመሪያ አንድ የቤተሰብ አባል ባ ለፉት 12 ወራት /ያለፉት 14 ቀናትን ጨምሮ/ ካልታመመ ወይንም ደግሞ በ አደጋ ምክንያት ጉዳት ካልደረሰበት ዓምዱ በሰረዝ /"_____"/ ሲታለፍ ሕመ ም/ጉዳት ደርሶበት የሕክምና ዕርዳታ ካላገኘ መልስ ኮድ "2" ካገኘ ደግሞ "1 " መሆን አለበት:: በመጀመሪያም በዓምድ 19 ወይም 25 ውስጥ "1" የሚል መልስ ለገባላቸው ሁሉ ዓምድ 29 ውስጥ "1" ወይም "2"

የሚል መልስ የተጻፈ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: "1" ወይም "2" የሚለ ው መልስ ትክክል መሆኑ የሚረጋገጠው ደግሞ ከዓምድ 30-38 ቢያንስ በአን ዱ ውስጥ "1" የሚል መልስ የተጻፈ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማገናዘብ ነ

ው። ከነዚህ ዓምዶች ቢያንስ በአንድ ውስጥ “1“ ተጽፎ ከተገኘ የሚመለከተ ው የቤተሰቡ አባል የሕክምና ዕርዳታ ማግኘቱን ስለሚያሳይ በዓምድ 29 ውስ ጥ “1“ የሚል መልስ መኖር እንዳለበት ተጨማሪ ማስረጃ ነው። ግን ከነዚህ ዓ ምዶች በአንዱም ውስጥ የሕክምና እርዳታ እንዳገኙ ካልተጠቀሰ ከሌሎች ዓም ዶች ጋር በማገናዘብ በዓምዱ “2“ ወይንም ደግሞ “______“ ሊገባለት የሚ ችል ሲሆን ከሌሎች ዓምዶች ጋር በማገናዘብ ሊስተካከል / ሊሞላ ካልተቻለ በ ዓምዱ ምንም የተጠቀሰ ነገር ከሌለ ያልተገለጸ ለማለት “9“ መጻፍ አለበት።

ዓምድ 30 - 38፡- ለዓምድ 29 መልሱ “1“ ከሆነ ከተዘረዘሩት ሕክምና አገኙ?

ለዓምድ 29 መልሱ “1“ ከሆነ ከነዚህ ዓምዶች ቢያንስ በአንዱ ውስጥ “1“ የሚል መልስ መጻፍ አለበት። ለአንድ የቤተሰብ አባል ለሁለት ወይንም ከዚያ በበለጡ ዓምዶች ውስጥ “1“ የሚል መልስ ሊገባለት ይችላል። በአጠቃላ ይም በነዚህ ዓምዶች ሊገቡ የሚችሉ መልሶች ከዓምድ 29 ጋር መገናዘብ አለባ ቸው። ለምሳሌ በአምድ 29 መልሱ “2“ ከሆነ ዓምድ 30 - 38 በሰረዝ ይታለ ፋል፣ መልሱ ከሆነ “1“ ከሆነ ደግሞ በዓምዶች “1“ ወይም “2“ የሚል መል ስ መጻፍ ይኖርበታል። በዓምድ 29 ወይም ዓምድ 28 መልሱ ሰረዝ “_____“ ከሆነ ዓምድ 30-38 በሰረዝ “______“ ይታለፋል።

ዓምድ 39፡- ለዓምድ 29 መልሱ “2“ /የለም/ ከሆነ ምክንያቱስ?

እንደ ብዙዎቹ ዓምዶች ሁሉ መረጃ ሰብሳቢው ይህን ዓምድ የሚሞላው በኮድ ነው። ለዚህ ዓምድ አማራጭ መልስ የሚሆኑት ኮዶች 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ ወይ ም 6 ናቸው። ይህም ዓምድ ተሞልቶ መገኘት ያበት ለዓምድ 29 የተሰጠው መልስ “2“ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ መጀመሪያ ይህ ሁኔታ ሳይሟላ በዓምድ 3 9 ውስጥ ኮድ ተጽፎ ሲገኝ፣ በስሕተት ሌላ መስመር መመዝገብ የሚገባው ሆ ኖ ሊታረም ካልሆነ በስተቀር፣ ትክክል ስላልሆነ መሰረዝ አለበት። ሁለተኛ - ለዓምዱ አማራጭ መልሶች ይሆናሉ ተብለው ከተሰጡት ኮዶች ሌላ ቁጥር በዓ ምዱ ውስጥ ያለመመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመጨረሻም በዓምዱ ምክ ንያት መገለጽ ሲገባው ሳይገለጽ ቢገኝ በዓምድ 29 መልሱ “2“ ሆኖ በዓምድ 39 ምንም ኮድ ሳይጻፍ/ወይም ከተሰጡት ኮዶች ውጭ የሆነ ቁጥር ቢመዘገብ ሰርዞ ያልተገለጸ ለማለት “9“ መጻፍ አለበት።

ዓምድ 40:- በዓምድ 30፣ 31፣ 32፣ 33 ወይም 34 መሠረት ካልታከሙ ምክንያቱስ?

ይህ ዓምድ ኤዲት የሚደረገው ከዓምድ 39 ጋር በተመሳሰለ ሁኔታ ነው:: አማራጭ መልስ የሆኑት ኮዶቹም አንድ ዓይነት ናቸው:: ነገር ግን ይህ ዓምድ ተሞልቶ መገኘት ያለበት ለዓምድ 29 መልሱ "1" ሆኖ ከዓምድ 30-34 የተሰጠው መልስ "2" ከሆነ ብቻ ነው:: ከዓምዱ ምንም ሳይጻፍ ቢመጣ ወይም ተገቢ ያለሆነ ኮድ ቢገኝ ማስተካከል ካልተቻለ ያለተገለጸ መሆኑ በኮድ "9" ይገለጻል::

ዓምድ 41 - 46 ዕድሜአቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ብቻ:-

ዓምድ 41:- ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ወልደዋል?

ዕድሜአቸው 15 ዓመትና በላይ የሆነች ማንኛዋም ሴት የበተሰብ አባል ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ መውለድ አለመውለዳቸው ከዚህ በታች በተመለከተው የኮድ አሰጣጥ መሠረት መመልከት ስለአለበት ይህንኑ አጣርቶ ካስፈለገም በማረም ማረጋገጥ ነው::

1 = አዎን/ ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ ለወለዱ ሁሉ/

2 = የለም/ » » » » ሳልወለዱ ሁሉ/

ዓምድ 42: - ለዓምድ 41 መልሱ "1" ከሆነ የመጨረሻውን ልጅ የት ነበር የወለዱት?

ይህ ዓምድ ተሞልቶ መገኘት ያለበት በዓምድ 41 ውስጥ ኮድ ለገባላቸው ሴቶች ብቻ መሆን አለበት:: ለዚህ ዓምድ አማራጭ መልስ የሚሆኑት ኮዶችም 1፣ 2፣ 3፣ 4 እና 5 ብቻ ናቸው:: በዓምድ 41 መልሱ "1" ሆኖ በዓምድ 42 ምንም ሳይጻፍ ቢመጣ ወይም ተገቢ ያለሆነ ኮድ ቢገኝ ማስተካከል ካልተቻለ ያለተገለፀ በመሆኑ ኮድ "9" ይገባለታል:: ሆኖም ይህ ዓምድ ኤዲት ሲደረግ ዓምድ 43-46 ካሉት መልሶች ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ኮዶቹም:-

1 = በራሳቸው /በሌላ ሰው መኖሪያ ቤት/

2 = ጤና ጣቢያ

3 = ክሊኒክ

4 = ሆስፒታል

5 = ሌላ

9 = ያልተገለፀ

ዓምድ 43:- ለዓምድ 41 መልሱ "1" ከሆነ የመጨረሻውን ልጅ ማን አዋለድዎት?

ይህ ዓምድ ልክ ዓምድ 42 ኤዲት በተደረገበት ዓይነት ኤዲተ ይደረጋል። ለዚህ ዓምድ ትክክለኛ አማራጭ ኮዶች 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5 እና 6 ናቸው። በዓምድ 41 ውስጥ ኮድ "1" ከተሞላ በዓምድ 42 የት እንደወለዱ የሚያመለክት ኮድ ለገባላቸው ሁሉ በዚህ ዓምድ ማን እንዳዋለዳቸው የሚገልጽ ኮድ መሞላት አለበት። ሌሎች ዓምዶች ኤዲት እንደተደረጉት ይህም ዓምድ ሳይሞላ ቢገኝ፣ ያልሆነ ኮድ ገብቶለት ቢገኝ ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ማስተካከል ካልተቻለ ያልተገለጸ የሚለው ኮድ / "9" / ይገባለታል። ኮዶቹም ከዚህ በታች ተመልክቷል።

1= የጤና ባለሙያ

2 = የቀበሌ ጤና ተጠሪ

3 = የሰለጠኑ ባህላዊ አዋላጅ፡

4 =ያለሰለጠኑ ባህላዊ አዋላጅ

5 = የማዋለድ ሙያ የሌላቸው

6 = ምንም አላዋለድንም

9 = ያልተገለፀ /በዓምዱ ምንም የገባ ኮድ ከሌለና ከሌሎች ዓምዶች ጋር አስተያይቶ ማስተካከል ካልተቻለ፣ እንደዚሁም ተገቢ ያለሆነ ኮድ ከተጻፈ/ ኮድ 9 ይሞላለታል።

ዓምድ 44:- ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ከወለዱ በመጨረሻው እርግዝናዎ ወቅት ዘመናዊ የህክምና እርዳታ አገኙ?

በዓምድ 41 ባለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ መውለዳቸው ለተገለጸላቸው ሁሉ /በዓምድ 41 መልሱ "1" ለተባለላቸው ሁሉ / በዚህ ዓምድ በመጨረሻው እርግዝናቸው ወቅት ዘመናዊ የሕክምና እርዳታ ማግኘታቸው/ አለማግኘታቸው ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካኝነት መገለጽ አለበት።

1= አዎን /ዘመናዊ የሕክምና እርዳታ ላገኙ ሁሉ/

2= የለም / » » » ላላገኙ ሁሉ/

9= ያልተገለጸ /በዓምዱ ምንም የገባ ኮድ ከሌለና ከሌሎች ዓምዶች ጋር አስተያይቶ ማስተካከል ካልተቻለ፣ እንደዚሁም ተገቢ ያለሆነ ኮድ ከተጻፈ/ ኮድ 9 ይሞላለታል።

<u>ዓምድ 45</u>:- <u>ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ከወለዱ በመጨረሻው እርግዝናዎ ወቅት የቲ.ቲ /T.T/ ክትባት ተደርጎልዎታል?</u>

በዓምድ 41 ውስጥ ያለው መልስ "1" ለተሞላላቸው ሴት የቤተሰብ አባላት ሁለ በዓምድ 45 በመጨረሻው እርግዝናቸው ወቅት የቲ.ቲ /T.T/ ክትባት የተደረገላቸው /ያልተደረገላቸው መሆኑ ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካኝነት መገለጽ አለበት።

1 = አዎን

2 = የለም

9 = ያልተገለጸ /በዓምዱ ምንም የገባ ኮድ ከሌለና ተገቢ ያለሆነ ኮድ

ከተጻፈ/ ኮለሞችን በማስተያየትና በመሳሰሉት ማስተካከል ካልተቻለ፣ 9 ይሞላለታል።

<u>ዓምድ 46</u>:- <u>ባለፉት 2 ዓመታት ልጅ ከወለዱ በመጨረሻ እርግዝናዎና እመጫትነትዎ</u>
_ <u>ወቅት በተጨማሪ ተመገቡ/ይመገባሉ?</u>

ቀደም ሲል በነበሩት ዓምዶች ኤዲት በተደረጉበት ተመሳሳይ መንገድ ይህን ዓምድ ከሌሎች ጋር በማመሳከር ኤዲት ይደረጋል። በዚህ ዓምድ የሚገበት አማራጭ መልሶች በአለፉት ሁለት ዓመታት ልጅ መውለዳቸው ለተገለጸላቸው የቤተሰቡ አባላት ሁሉ ተጨማሪ ምግብ /በእርግዝናና እመጫትነታቸው/ ማግኘት አለማግኘታቸውን ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካኝነት መገለጽ ይኖርበታል።

0= በእርግዝና እና በእመጫትነት ወቅት በተጨማሪ ላልተመዘገቡ፣

1= በእርግዝናቸው ወቅት ብቻ በተጨማሪ ለተመዘበ፣

2= በእመጫትነትዎ ወቅት ብቻ በተጨማሪ ለተመገቡ፣

3= በእርግዝናቸውና በእመጫትነታቸው ጊዜ በተጨማሪ ለተመገቡ፣

9= ያልተገለጸ /በዓምድ 41 መልሱ "1" ሆኖ የአመጋገባቸው ሁኔታ ላልተገለጸ ወይም ትክክለኛ ኮድ ላልገባላቸው እና ኮለሞችን በማስተያየት ማስተካከል ካልተቻለ/

## ክፍል 3 :- የሕፃናት ክብደትና ቁመት ልክቶች፣ የአመጋገብና የክትባት ሁኔታ (ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሁሉ)

### ዓምድ 47 :- የህፃኑ ተራ ቁጥር (ከክፍል 2 ዓምድ የሚወራረስ)

በዚህ ዓምድ የህፃኑ ተራ ቁጥር ከክፍል ዓምድ 11 በመውሰድ በመረጃ ሰብሳቢ ው የሚወራረስ ነው:: ከዚህ ዓምድ በፊትና በኋላ ያሉ የሕፃኑን መረ ጃ ለመጠቀም የሚቻለው ይህ ዓምድ በትክክል ተሞልቶ ሲገኝ ነው:: በመሆኑ ም ኤዲት በሚደረግበት ወቅት የማወራረሱ ተግባር በትክክል የተከናወነ መሆ ኑን ማረጋገጥ እና በትክክል ካልተወራረሰ የህፃኑን ስምና የወላጅ እናትን ተራ ቁጥር በማስተያየት ማስተካከል ያስፈልጋል:: ይህ ዓምድና ሌሎች ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆናቸው ብቻ መሆኑን ማ ጤን ተገቢ ነው::

### ዓምድ 48 :- የህፃኑ ሙሉ ስም

ይህ ዓምድ የሚሞላው ዕድሜው ከአምስት ዓመት በታች ለሆናቸውና በዓምድ 47 ተራ ቁጥር ለተሰጣቸው ህፃናት ነው:: በዓምድ 48 የተሟላውን መረጃ በ ክፍል 2 ዓምድ 12 ውስጥ በመደበኛ ቤተሰብ አባላት ከተመዘገበው የህፃኑ ስ ም ጋር አንድ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

### ዓምድ 49 :- የህፃኑ ወላጅ እናት ተራ ቁጥር

በክፍል 2 ዓምድ 12 በተዘረዘሩት መደበኛ የቤተሰብ አባላት መካከል በዓምድ 48 ለተመዘገበው ህፃን ወላጅ የሆኑት ተራ ቁጥር ከክፍል 2 ዓምድ 1 1 ተወስዶ ይመዘገባል:: በዓምድ 49 የተመዘገበው መረጃ በትክክል ከተባለው ዓምድ መወሰዱን እና ከቤተሰቡ ለልጁ እናት ሊሆኑ የማይችሉ አባል ማለት ለአቅመ ሔዋን ላልደረሱ ህፃናት እና ለወንዶች የተሰጠ ተራ ቁጥር አለመሆኑ ን በማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ማስተካከል ተገቢ ነው::

### ዓምድ 50 :- የህፃኑ ዕድሜ (በሙሉ ወራት)

ከዚህ ዓምድ በስተቀር በክፍል 2 ዓምድ 14 የተመዘገበው ዕድሜ በሙ ሉ ወራት ነው:: በዚህኛው ዓምድ ግን በሙሉ ወራት ብቻ መመዝገብ አለበት :: በኤዲቲንገ ወቅት በመጀመሪያ ደረጃ በዓምዱ የተሞላው ዕድሜ ከ59 ወራ ት ሊበልጥ እንደማይችል ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም በዚህ ክፍል መረ

ጀ የሚሞላላቸው ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆናቸው ብቻ ስለሆነ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ በዓምዱ የተሞላውን በዓምድ 14 ካለው ጋር በማመሳ ከር በዓምድ 14 የተሞላውን ወደ ወራት በመቀየር በዓምድ 50 ውስጥ ከተመ ዘገበው ጋር እኩል ወይም የሚያንስ መሆኑን ማረጋገጥ ማለት ነው:: ይህም ማ ለት ዓምድ 14 ውስጥ በሙሉ ዓመት ስለሚመዘገብ እና ከዓመት የተረፈ ወራ ት ስለሚጣሉ ፡ በዚህኛው ግን ህፃኑ የጨረሰው ዕድሜ በሙሉ ወራት ስለሚ መዘገብ ከዓምድ 50 ሊበልጥ አይችልም:: ከዚህ ሌላ ሁለቱን ዓምዶች በማገናዘ ብ መረጃውን ማስተካከል ተገቢ ነው::

<u>ዓምድ 51</u> :- <u>ህፃኑ ለእናቱ ስንተኛ ልጅ ነው?</u>

ከዓምድ 47-50 መረጃ የተሞላለት ህፃን ለወላጅ እናቱ ስነተኛ ልጅ እንደሆነ ተጠይቆ የሚመዘገብበት ዓምድ ነው:: በዚህ ዓምድ የሚሞላው መረ ጃ እንደየሁኔታው ከ«1»፣ «2»፣ «3»፣ «4»፣ «5»፣ «6»፣ «7»፣ እና «8» ብቻ ነው:: በመመሪያው መሠረት ህፃኑ ለእናቱ 9ኛ ወይም ከዚያ በላይ ሲሆን በዓምዱ ተመዝግቦ ከሆነ ከሌሎች መረጃ ማለት የእናቱ ዕድሜ በቤተሰቡ ው ስጥ ያሉት ህፃናት ዕድሜ መራራቅና የህፃናት ብዛት ጋር በማዛመድ ማረም ካ ልተቻለ 8ቻ ተብሎ ይታረማል ማለት ነው:: ቁጥሩ ከ8 በታች ቢሆንም ከሌላ ው መረጃ ጋር በማገናዘብ ትክክለኛነቱን ለማጣራት መሞከር ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 47-67</u>:- <u>ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆነ ሕፃናት ብቻ</u>:-

በመጀመሪያ በዓምድ 47 - 55 መረጃ የተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ ዕ ድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው:: ለማይመለከ ታቸው የቤተሰቡ አባላት እነዚህ ዓምዶች በሰረዝ " ___ " ይታለፋሉ::

<u>ዓምድ 52-55</u>:- <u>ሕፃናት ከተወለዱ ጀምሮ ለሚከተሉት ክትባት ተደረገላቸው?</u>

ዕድሜአቸው ከ " አምስት " ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ከተወለዱ ጊዜ ጀም ሮ ለአንዳንድ በሽታዎች መከላከያ የሚሆኑ ክትባቶች መውሰዳቸውን/ አለመው ሰዳቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች በነዚህ ዓምዶች ውስጥ ተሰብስቧል:: መረጃ ዎቹም ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች ብቻ መገለፃቸውን ካስፈለገም በማረም ማረ ጋገጥ አለበት::

ዓምድ 52:-  1 = የኩፍኝ ክትባት ለተከተበ፡፡

2 = የኩፍኝ ክትባት ላልተከተበ፡፡

9 = መከተብ አለመከተባቸው ሳይገለፅ ሲቀር፡፡

ዓምድ 53:-  1 = የቢ.ሲ.ጂ. ክትባት ለረከተበ፡፡

2 = የቢ.ሲ.ጂ. ክትባት ላልተከተበ፡፡

3 = መከተብ አለመከተባቸው ሳይገለፅ ሲቀር፡፡

ዓምድ 54:-  1 = የዲ.ፒ.ቲ ክትባት ለተከተበ፡፡

2 = የዲ.ፒ.ቲ ክትባት ያልተከተበ፡፡

9 = መከተብ አለመከተባቸው ላልተገለጸላቸው፡፡

ዓምድ 55:-  1 = የልምሻ (polio) ክትባት ለተከተበ፡፡

2 = የልምሻ (polio) ክትባት ላልተከተበ፡፡

3 = መከተብ አለመከተባቸው ሳይገለፅ ሲቀር፡፡

በመቀጠልም እነዚህ ኮዶች በሕፃኑ ስም ትክክል መጻፋቸውን ማረጋገጥ ምናልባት በስም ትክክል መረጃዎች ሳይቀመጡ ቢገኙ ማስተካከል አስፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻ እነዚህ ዓምዶች ምንም ቁጥር ሳይሞላባቸው ቢገኙ ወይንም ደግሞ ተገቢ ያልሆነ ኮድ ተጽፎ ቢገኝ ሁኔታዎችን ማስተካከል ተስማሚውን ኮድ ማግኘት ካልተቻለ ሁኔታው ያልተገለጸ ስለሆነ ይኸው በዓምድ ኮድ “9” ን በማስገባት ይገለጽ፡፡

ዓምድ 56:-  ህፃኑ ቫይታሚን ኤ እንክብሎች ወስዷል?

ህፃኑ የቫይታሚን ኤ እንክብሎች ወስዶ ከሆነ ኮድ «1» ያልወሰደ ከሆነ ኮድ «2» በዚህ ዓምድ ይሞላል፡፡ ያልተገለፀ ከሆነ ኮድ 9 ይሞላለታል፡፡

ዓምድ 57:-  ህፃኑ ባለፉት 14 ቀናት ተቅማጥ ትውከት ሳል ታሞ ነበር?

ባለፉት 14 ቀናት የተጠቀሰው ሕፃን በተቅማጥ በትውከት ወይም በሳል ታሞ የነበር ከሆነ ተጠይቆ የሚመዘገብበት ዓምድ ነው፡፡ ለዚህ ዓምድ የተሞላውን መረጃ በዓምድ 19 ከተሞላው ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡በዚህኛው ዓምድ ታሟል ተብሎ ኮድ «1» ከተመዘገበ በዓምድ 19 ኮድ «2» ሊሆን አይቻልም፡፡

ምክንያቱም ሁለቱም ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ስለነበረው የህፃኑን የጤንነት ሁኔታ የሚመለከቱ ናቸው:: ላልተገለፀ ኮድ «9» ይመዘገብለታል::

ዓምድ 58:- ከዓምድ 47 መልሱ «1» ከሆነ ምን ወስዶ ነበር?

በዓምድ 57 ታሟል ተብሎ ኮድ «1» ለተሞላላት ህፃን ብቻ የሚሞላ ነው:: በ ዓምድ 57 የተሞላው መረጃ ኮድ «2» ከሆነ ይህ ዓምድ አይጠየቅም:: በሥረዝ ይታለፋል:: ነገር ግን የተሞላው ኮድ «2» ከሌሎች ተዛማጅ መረጃ ጋር ሲመሳከር ስህተት ከሆነ አስፈላጊውን እርምት ማድረግ ያስፈልጋል:: በዓምዱ ሊመዘገቡ የሚችሉ ኮዶች:-

1= ኦ አር ኤስ (O.R.S)

2 = ቤት የተዘጋጁ ሌሎች ፈሳሽ ምግቦችና ሌሎች ፈሳሾች

3= ሌላ መድኃኒት

4= 1 + 2

5= ምንም አልተሰጠውም

9= ያልተገለጸ/በዓምዱ ምንም የገባ ኮድ ከሌለና ከሌሎች ዓምዶች ጋር አስተያይቶ ማስተካከል ካልተቻለ፣ እንደዚሁም ተገቢ ያለሆነ ኮድ ከተጻፈ/ ኮድ 9 ይሞላለታል::

ዓምድ 59:- ህፃኑ እንደተወለደ ምን ተሰጠው?

በጥናቱ በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ በአባልነት ያሉ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆነችው በሙሉ በዚህ ዓምድ ሲወለዱ ወዲያውኑ የተሰጣቸው ምን እነደሆነ ተጠይቆ የሚመዘገብበት ዓምድ ነው:: አማራጭ ኮዶቹም:-

1= የእናት ጡት ወተት ብቻ

2 = ሙቅ ውሃ

3= ጥሬ ቅቤ

4= አብሽ

5= የእንስሳት ወተት/ሌላ ወተት

6= ሌላ

9= ያለተገለጸ/ ምን እንደተሰጣቸው ላልተገለጸ ወይመ ሊገለጽ ያልቻለ /

በዚሁ መሠረት የተሞላው ኮድ ባለ አንድ ድጅት መሆኑን ማረጋገጥና በፊደል ተጽፎ ከሆነ ሰርዞ በትክክለኛው ኮድ መተካት ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 60:- ህፃኑ እንደተወለደ የእናቱን ጡት መጥባት የጀመረበት ዕድሜ /በሰዓት/

ዕድሜው ከአምስት ዓመት በታች ለሆናቸውና በተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ በ አባልነት የሚገኙ ህፃናት በሙሉ እንደተወለዱ የእናታቸውን ጡት መጥባት የ ጀመሩበት ሰዓት ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካኝነት በዓምዱ ውስጥ መሞላ ቱን ማረጋገጥ ካስፈለገም በማረም መስተካከል ይኖርበታል፡፡

01 = ከ1 ሰዓት በታች

02 = ከ1-6 ሰዓት

03 = 7-12 ሰዓት

04 = 13-24 ሰዓት

05 = 25-48 ሰዓት

06 = ከ48 ሰዓት በላይ

07 = ጭራሽ አልጠባም

09 = ያልተገለጸ/ በስንት ሰዓት ጡት መጥባት እንደጀመሩ ላልተገለፀ ወይም ሊገለጽ ያልቻለ/

ዓምድ 61:- በአሁኑ ጊዜ ሕፃኑ ጡት ይጠባል?

ዕድሜው ከአምስት ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም የቤተሰብ አባል ጥናቱ በማ ካሄድበት ጊዜ ጡት የሚጠባ ወይም የማይጠባ መሆኑን ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካኝነት በዓምዱ መገለጹን ካስፈለገም በማረም መረጋገጥ አለበት፡፡

1= አዎን ጡት ለሚጠቡ ሁሉ/

2= የለም/ጡት ለማይጠቡ ሁሉ/

9= ያልተገለጸ /ጡት የሚጠቡ ወይም የማይጠቡ መሆናቸውን ላልተገለጸ ወይም ሊገለጽ ላልቻለ/፡

ይህ ዓምድ ኤዲት በሚደረግበት ጊዜ በተለይ ከዓምድ 53 እና ቀጥሎ ካሉት ዓምዶች ጋር የሚገናዘብ መሆኑን ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በዓምድ 62 ጡት መጥባት አቁሟል ተብሎ ህፃኑ ጡት ማጥባት ያቆመበት ወር ለተገለጸለት ሕፃን በዓምድ 61 ያለው መልስ በምንም ዓይነት "1" ሊሆን አይችልም ።

ዓምድ 62:- <u>ካልጠባ/ካልጠባች መጥባት ሲያቆም/ሳታቆም ዕድሜው/ዋ ስንት ወሮች ነበር?</u>

ከሁሉ በፊት እዚህ ዓምድ ውስጥ የተሞሉት ቁጥሮች ባለ ሁለት ዲጂት መሆናቸውና እነዚህ ቁጥሮች ከ "00" ጀምሮ "01"፣ "02"፣ እያሉ በመቀጠል እስከ "59" ሊደርሱ መቻላቸው በስተቀር ከ "59" የበዛ ቁጥር ያለመጻፉ መረጋገጥ አለበት። ከዚህ የተለየ አሞላል ካለ መስተካከል አለበት። ምናልባት ሕፃኑ መጥባት ያቆመበት ዕድሜ ካልተፃፈ ግን ያልተገለፀ ለማለት "99" ይጻፋል። በተጨማሪም በዓምድ 61 ውስጥ "2" የሚል መልስ ለተጻፈላቸው ሕፃናት ብቻ ጡት መጥባት ያቆሙበት ወራት መጻፉ መረጋገጥ አለበት።

ዓምድ 63:- <u>ባለፉት 4 ሳምንታት ለህፃኑ የተሰጠው የምግብ ዓይነት</u>

በጥናቱ ለተሸፈኑ ህፃናት በሙሉ ወላጅ እናቶቻቸውን በመጠየቅ ባለፉት 4 ሳምንታት ህፃኑ በአብዛኛው ይመገብ የነበረው ምን እንደሆነ የሚገልጽ መረጃ በዓምዱ ይሰበሰባል። የእናቱን ጡት ብቻ ለሚወስድ የእናት ጡት ብቻ የሚለውን ኮድ "0" የእናቱን ጡት እየጠባ ባለፉት 4 ሳምንታት ምግብ ሲወስድ ለነበረ በተጨማሪ የወሰደውን የምግብ ዓይነት የሚገልጸውን ኮድ በመጠይቁ ዓምድ 63 ግርጌ እና ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አማራጮች በመምረጥ የተገለጸው መሆኑን ካስፈለገም በማረም መረጋገጥ አለበት።

1 = የእናት ጡት ወተት ብቻ፣
2 = የእንስሳት ወተት/ሌላ የእንስሳት ውጤት፣
3 = ጥራጥሬ፣
4 = አትክልት /ፍራፍሬ/ ሌላ ሥራ ስር፣
5 = 1+2 ወይም 1+3 ወይም 1+ 4፣
6 = 2+3 ወይም 2+4፣
7 = 3+4፣
8 = ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ / ድብልቆች፣
9 = ያልተገለጸ /በዓምዱ ምንም የገባ ኮድ ከሌለና ከሌሎች ዓምዶች

ጋር አስተያይቶ ማስተካከል ካልተቻለ፤ እንደዚሁም ተገቢ ያለሆነ ኮድ ከተጻፈ/ ኮድ 9 ይሞላለታል።

<u>ዓምድ 64፤</u> <u>ለዓምድ 63 መልሱ «1» ከሆነ ከእናቱ ጡት በተጨማሪ ሌላ ምግብ መ መገብ ሲጀምር/ስትጀምር ዕድሜው/ዋ ስንት ወራት ነበር?</u>

ከሁሉ በፊት እዚህ ዓምድ ውስጥ የተጻፈው በዓምድ 63 ውስጥ "1" የሚል መልስ ለተጻፈላቸው ሁሉ እና ምናልባትም ካልተገለፀላቸው ሕፃናት መካከል ለአንዳንዶቹ ብቻ መሆኑ ካስፈለገም በማረም መረጋገጥ አለበት። ከዚያም የተ ሞሉት ቁጥሮች ባለ ሁለት ዲጂት መሆናቸውንና ከ "00" ጀምሮ እስከ "59" ያለ ቁጥር ብቻ መሆናቸውን ካስፈለገም በማስተካከል መረጋገጥ ይኖርበታል ። ምናልባት የሕፃኑ ዕድሜ ካልተጻፈ ደግሞ ሁኔታውን በሌላ መንገድ ማወቅ ካልተቻለ ያልተገለፀ ለማለት "99" መጻፍ አለበት።

እዚህ ላይ በድጋሚ መታወስ ያለበት ለሕፃኑ በዓምድ 51 ተጨማሪ ም ግብ እንደሚመገብ ኮድ "1" በማስገባት ከተገለጸ በዚህ ዓምድ በመጀመሪያ ከ እናቱ ጡት ሌላ ምግብ መመገብ የጀመረበት ዕድሜ በወር መመዝገብ እንዳለ በት ይጠቁማል። በተጨማሪም በዚህ ዓምድ /ማለትም በዓምድ 64/ የተሞላው የወራት ብዛት 53 ከተሞላው ቢያንስ ወይም ቢበዛ እኩል ይሆናል እንጂ በ ምንም ዓይነት ሊበልጥ ስለማይችል፤ ይኸ በጥሞና ተስተውሎ መረጋገጥ ይኖርበ ታል።

<u>ዓምድ 65፡-</u> <u>ስለሕፃኑ የእድገት ሁኔታ የእናቱ አስተያየት</u>

በዚህ ዓምድ ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆናቸው ሁሉ ስለ ዕድገ ት ሁኔታቸው የእናታቸው አስተያየት ቀጥሎ በተመለከቱት ኮዶች አማካይነት ይገለፃል። በተጨማሪ የዕድገቱ ሁኔታ በኮድ ሳይገለጽ ከቀረ ወይም መግለጽ ካ ልተቻለ ኮድ «9» ይገባለታል።

1 = ትክክለኛ ዕድገት ነው

2 = ትክክለኛ ዕድገት ያለሆነ ነው

3 = አያውቁም

9 = ያልተገለጸ/በዓምዱ ምንም የገባ ኮድ ከሌለና ከሌሎች ዓምዶች ጋር አስተያይቶ ማስተካከል ካልተቻለ፤ እንደዚሁም ተገቢ ያለሆነ

ኮድ  ከተጻፈ/ ኮድ 9 ይሞላለታል።

<u>ዓምድ 66-67፡-</u>  <u>ዕድሜአቸው ከ3 ወር እስከ 5 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ብቻ፡-</u>

እነዚህ ዓምዶች የሕፃናት የቁመትና ክብደት ልኪቶሽ የሚደረጉላቸው ሕፃናት ዕድሜአቸው ከ3 ወር እስከ 5 ዓመት በታች /ማለት 3 ወር - 4 ዓመት 11 ወር/ የሆነ ብቻ መሆን ስላለበት በዓምድ 9 ውስጥ ስማቸው ከተመዘገበው ሕፃናት መካከል ዕድሜአቸው ከ3 ወር በታች ለሆናቸው እነዚህ ዓምዶች ውስ ጥ ልኪቶች የተመዘገበላቸው መሆኑ በትክክል ማረጋገጥና በተጨማሪም ልኪቶቸ ለማይመለከታቸው ሕፃናት መሞላቱ ከተረጋገጠ እነዚህን ልኪቶች መሰረዝ ነው። ከመሰረዛቸው በፊት የተሞላው መረጃ ሌሎችን ሳይሆን በእርግጥ እነዚህ ን ከ3 ወር በታች የሆናቸውን ህፃናት ብቻ የሚመለከቱ ልኪቶች መሆናቸው መረጋገጥ አለበት።

<u>ዓምድ 66</u>- <u>ቁመት በሴንቲ ሜትር፡</u>-

እዚህ ዓምድ ውስጥ ደግሞ ዲሲማል ነጥብ መኖር የሌለበት መሆኑንና የሚጻፈ ውም ቁጥር ባለ ሦስት ዲጂት መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳ ሌ የልኪቱ መጠን 75 ወይም 94 ወይም 106 ሲሆን መጻፍ ያለበት ቁጥር 0 75፣ 094 ወይም 106 ነው። ስለዚህ የሚታዩት ስህተቶች በነኚህ ነጥቦች መሠ ረት መስተካከል ይኖርባቸዋል። ምናልባት ለሚመለከተው ሕፃን ምንም የቁመ ት ልኪት ያለመጻፉ ከተረጋገጠ ያልተገለፀ ለማለት “999” መሞላት አለበት።

<u>ዓምድ 67፡</u>- <u>የሕፃኑ ክብደት (በግራም)፡</u>

እንደ ዓምድ 67 እዚህ ዓምድም ውስጥ መጻፍ ያለበት ቁጥር ባለ አም ስት ዲጂት ቁጥር መሆን እንደሚኖርበት መገንዘብ ያሻል። ለምሳሌ የልኪቱ መጠን 7፣ 9፣ 11 ወይም 16.0 ቢሆን መጻፍ ያለበት 07.000፣ 09.000፣ 11.0 00 ወይም 16.000 ነው። እንደዚሁም የልኪቱ መጠን ከ “04.0” ኪሎ ግራም አቅራቢያ ሊያንስ ከ “18.5” ኪሎ ግራም ገደማ ደግሞ ሊበልጥ የማይችል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ምናልባት ለሚመለከተው ሕፃን ምንም አይነት የክብደት ልኪት ያለመ ሰጠቱ ከተረጋገጠ ያልገተለፀ ለማለት “99999” መሞላት አለበት።

# <u>የወሊድ እና የሞት ሁኔታ</u>

<u>ክፍል 1</u>:- <u>የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ</u>

ለአንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ መጠይቆች ከተሞላለት በመጀመሪያው መጠይቅ በዓምድ 1-10 የተሞሉት የአካባቢ መለያ መረጃዎች ሁሉ ለቤተሰቡ በተሞሉት መጠይቆች ሁሉ እንዳሉ ተደግመው መጻፋቸው መረጋገጥ አለበት: : በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓምድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳ ከር ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 1-7</u>:- በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ መጻፍ ያለባቸው ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰ ብ የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ/ከፍተኛ ቀበሌ/ገ/ማህበር እና የቆጠራ ቦታ ስም ናቸው:: ስለዚህ መጀመሪያ እነኚህ ዓምዶች አንድም ሳይዘለል በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ነው:: ከነዚህ ዓምዶች አንዱ ሳይሞላ ቢቀር በሌሎች ዓምዶች ውስጥ ከተመዘገቡት መረጃዎች ጋር በማመሳከር መሞላት አለበት:: ለምሳሌ በዓምድ 1 ውስጥ የክልል ስም እና በዓምድ 3 ውስጥ የወረዳ ስም ተ መዝግቦ በዓምድ 2 ውስጥ የዞን ስም ባይሞላ የክልሉንና የወረዳውን ስም በማ የት የዞን ስም ለይቶ መጻፍ ይቻላል:: ከዚያም በነዚህ ዓምዶች ውስጥ የሰፈረ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ/ከፍተኛ፣ ቀበሌ/ ገ/ማህበር ስም ሁሉ የቦታዎችን ስም ኮድ ለማድረጊያ በተዘጋጀው የኮድ ዝርዝር ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈል ጋል:: በመጨረሻም በኮድ ዝርዝሩ መሠረት በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ ኮድ ለማ ድረጊያ በተመደቡት ቦታዎች/ካርድ ኮለሞች/ ውስጥ ትክክለኞቹ

ኮዶች ይሞሉላቸዋል:: በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓምድ ከ ተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 8</u>:- <u>የተመረጡ ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር</u>:-

በዓምድ8 የተሞላው የምርጫ ተራ ቁጥር ባለ ሁለት ዲጂት ሆኖ በት ክክል መስፈሩንና ቁጥሩ በደንብ የሚነበብ መሆኑን ማረጋገጥ ነው:: ለጤናና አመጋገብ ጥናት የሚመረጡ ቤተሰቦች 25 ስለሆነ በዚህ ዓምድ የሚመዘገበው ቁጥር ከ25 መብለጥ የለበትም:: በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓም ድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 9</u>:- <u>የቤተሰብ አባላት ብዛት</u>

በዚህ ዓምድ ውስጥ የቤተሰብ አባላት ብዛት ተመዝግቧል። በዚህ ዓም ድ የተመዘገበው መረጃ ከዓምድ 12 /የመደበኛ ቤተሰብ አባላት/ ጋር የሚዛ መድ በመሆኑ በሁለቱ ዓምዶች ላይ የሰፈረው የአባላት ብዛት ተመሳሳይ መሆ ን አለበት። ካልሆነ በኤዲቲንግ መስተካከል ይኖርበታል። በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓምድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 10:- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም</u>

በዚህ ዓምድ የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም ተመዝግቧል። በዚህ ዓምድ የ ተመዘገበው ስም በዓምድ 12 ከሰፈረው ስሞች መካከል ከአንዱ የአባላት ስም ጋር አንድ መሆን ይኖርበታል። በ ጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓም ድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

<u>ክፍል 2:- የወሊድ እና የሞት ሁኔታ</u>

<u>ዓምድ 11:-</u> <u>ተራ ቁጥር:-</u> በዚህ ዓምድ ከ01 እስከ 10 የቤተሰብ አባላት መመዝገብ የሚችል አስቀድሞ ተሞልቷል። በመጀመሪያው መጠይቅ ላይ 10 ሰዎች ከተ መዘገቡ የቤተሰቡ አባላት የተመዘገቡበት ሌላ ተከታይ መጠይቅ መኖሩ ወይም አለመኖሩ መረጋገጥ አለበት። ከአንድ መጠይቅ በላይ ለቤተሰቡ መጠቀሙ ከ ታወቀ በሁለተኛው መጠይቅ ተራ ቁጥር 01 ሳይሆን ከ11 መጀመር አለበት። እንዲሁም ሌሎች ቀጣይ ተራ ቁጥሮች በ02 ፈንታ 12፣ በ03 ፈንታ 13፣ ... ወዘተ እያለ እስከ መጨረሻው መቀጠሉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመጨረሻ ለተመዘገበ የቤተሰብ አባል የተሰጠው ተራ ቁጥር በጠቅላላ ከአሉት ከቤተሰቡ አባላት ብዛት ጋር እኩል መሆን አለበት። በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳ ሳይ ዓምድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 12:-</u> <u>መደበኛ የቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም:-</u>

ይህ ዓምድ ኮድ አይደረግም።

ዓምዱ ሌሎች ዓምዶች በሚታረሙበትና ኮድ በሚሰጣቸው ጊዜ ለማመ ሳከር ይጠቅማል። በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓምድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 13:-</u> <u>ፆታ:-</u>

እዚህ ዓምድ ውስጥ የያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ፆታ በኮድ/1

ወይም 2 መሆኑ/ መገለጽ አለበት። ስለዚህ መጀመሪያ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል “1” ወይም “2” የሚል መልስ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከዚያም “1” የሚለው መልስ ወንድ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ብቻ “2” የሚለው ኮድ ደግሞ ሴት ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ብቻ መመዝገቡን ቀጥሎ በተጠቀሱት ዘዴዎች ማረጋገጥና ካስፈለገም ማረም ነው።በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓምድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

እነዚህም የሚረጋገጡት በዓምድ 12 ውስጥ ከሠፈረው ስማቸው፣ ዕድሜአቸው ከ15 ዓመት በላይ ለሆኑ ሴቶች በዓምድ 41-46 ስለ ወሊድ ተጠይቀው እንደሆነ በማመሳከር እና በማዛመድ ነው። በተጨማሪም በዓምድ 20 እና 21 ከሠፈሩት በሽታዎች መካከል አንዳንዶቹ ከሴቶች ላይ ብቻ የሚታዩ ስለሆነ አንዳንድ አባላት ሴት ስለመሆናቸው ተጨማሪ ማረጋገጫ
ሊሆኑ ይችላሉ ለምሳሌ ውስብስብ እርግዝና፣ ውርጃ፣ አስቸጋሪ ወሊድ፣ ... የሴቶች የጤና መታወክ ናቸው።

አልፎ አልፎ ምናልባት የእያንዳንዱ ሰዎች ጾታ ካልተሞላ ከላይ በተዘረዘሩት ዓምዶች ውስጥ የተሠጡትን መልሶች በማገናዘብ ጾታውን ማወቅ ስለሚቻል ትክክለኛውን ኮድ መጻፍ ነው።

<u>ዓምድ 14:- ዕድሜ በሙሉ ዓመት:-</u>

የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ በካርድ ኮለም 26 እና 27 ውስጥ በሙሉ ዓመት ብቻ መመዝገብ አለበት። የዕድሜ አመዘጋገብ ዓመት ከ«00» እስከ «97»፣ የተመዘገበ ነው። ስለሆነም ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆኑ አባላት ዓመት 01፣ 02፣ 03፣ 04፣ 05፣ 06፣ 07፣ 08፣ እና 09 ሲመዘገብላቸው ዕድሜያቸው 98 እና በላይ ለሆኑት አባላት ግን «97» ብቻ ተብሎ መፃፍ አለበት። ዕድሜው ከ97 ዓመት በታች ለሆነ ሌላ ዕድሜ ላለው አባል ግን ያው ዕድሜው እንዳለ በሙሉ ዓመት ይጻፍለታል። በተጨማሪም በአጠቃላይ የማንኛውም አባል ዕድሜ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሌሎች አባለት/ወላጆች፣ ልጆች፣ . . . .ወዘተ/ ከተመዘገቡት ዕድሜዎች ጋር ማመሳከር ያስፈልጋል። በተለይ ዕድሜያቸው ያልተመዘገበ አባለት ሲያጋጥም በዚህ ዘዴ ዕድሜያቸው ያልተመዘገበ አባላት ሲያጋጥም በዚህ ዘዴ ዕድሜያቸውን ገምቶ ለመ

መዝገብ መሞከር ያስፈልጋል። ዕድሜው በምንም ዓይነት ሊታወቅ ላልቻለ አባ ል ግን «99» ይጻፋል። በጤናና አመጋገብ ጥናት በተመሳሳይ ዓምድ ከተሞ ላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 15፡-</u> <u>የጋብቻ ሁኔታ፡-</u>

ለእያንዳንዱ ዕድሜው 15 ዓመት ወይም በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል የጋብቻ ሁኔታ ከዚህ በታች በተመለከተው የኮድ አሠጣጥ መሠረት እዚህ ዓም ድ ውስጥ በኮድ መስፈር አለበት።

1= አግብተው የማያውቁ

2= በትዳር ላይ ያሉ

3= የተፋቱ

4= የሞተባቸው

ስለዚህ መጀመሪያ በዓምዱ ውስጥ 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ የሚል መልስ የተጻፈ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪም በጤናና አመጋገጥ ክፍል 2 ዓምድ 18 ውስጥ ከተመዘገበው መረጃ ጋር ማገናዘቡ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ በሁለቱ ዓምዶች የተሞላው መረጃ ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆ ናቸው ሁሉ የግድ ተመሳሳይ መሆን አለበት። በጤናና አመጋገብ ጥናት በተ መሳሳይ ዓምድ ከተሞላው መረጃ ጋር መመሳከር ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 16-21</u> <u>ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ሴቶች ብቻ የሚሞላ</u>

በእነዚህ ዓምዶች የሚሞላው መረጃ በዕድሜና በፆታ የተገደበ በመሆኑ ዕድሜ ያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆናቸው እና ለወንዶች አለመሞላቱን ከሌሎች ዓ ምዶች ጋር በማገናዘብ ማረጋገጥ ካስፈለገም በማረም ማስተካከል ያስፈልጋል።

<u>ዓምድ 16 ፡-</u> <u>በጠቅላላ በሕይወት የወለዷቸው ልጆች ብዛት ስንት ናቸው?</u>

ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች በሕይወት ከወለዷቸ ው ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻቸው ውስጥ እቤት የሚኖሩ በፆታ በመለየት ወን ዶች ስንት እንደሆኑ በዓምድ 16 በንዑስ ዓምድ 29 እና እቤት የሚኖሩ ሴቶ ች ደግሞ ስንት እንደሆኑ በንዑስ ዓምድ 30 ይሞላል። በንዑስ ዓምድ 31 እና 32 ይሞላል። ከዚህ ሌላ ይህ ዓምድ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆናቸ

ው ሴቶች እና ለወንዶች ያልተሞላ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከ ሌሎች ዓምዶች ጋር በማስተያየት እና በማገናዘብ ማስተካከል ተገቢ ነው።

ዓምድ 17 :- በጠቅላላ በሕይወት ከወለዷቸው ልጆችው ውስጥ ሌላ ቦታ የሚኖሩ ስንት ናቸው?

ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች በሕይወት ከወለዷቸው ወንዶ ች እና ሴቶች
ልጆቻቸው ውስጥ ሌላ ቦታ የሚኖሩ ወንዶች ስንት እንደሆኑ በዓምድ 17 በንዐ -ስ ዓምድ 31 ሌላ ቦታ የሚኖሩ ሴቶች ስንት እንደሆነ በንዑስ ዓምድ 32 ይሞላል።

ዓምድ 18 :- በጠቅላላ በሕይወት ከወለዷቸው ልጆች ውስጥ የሞቱ ልጆች ስንት ናቸው?

ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች በሕይወት ከወለዷቸ ው ወንዶች እና ሴቶች
ልጆቻቸው ውስጥ የሞቱ ወንዶች ስንት እንደሆኑ በዓምድ 17 በንዑስ ዓምድ 33 የሞቱ ሴቶች ስንት እንደሆነ በንዑስ ዓምድ 34 ይሞላል።

ዓምድ 19 :- በጠቅላላ በሕይወት ከወለዷቸው ልጆች ስንት ናቸው?

በዓምድ 19
ደግሞ በጠቅላላ በሕይወት ከወለዷቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆች (በፆ ታ ሳይለይ) ውስጥ ስንት
እንደሆነ ተጠይቆ በንዑስ ዓምድ35 እና36 የሚሞላበት ነው።

ማሳሰቢያ ዓምድ 16፣ 17 እና 18 ላይ የተሞሉት ተደምረው ዓምድ 19ን መስጠት አለባቸው።ድምራቸው እኩል የማይሆን ከሆነ ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ይከናወናል።

ዓምድ 20 :- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ልጅ ከወለዱ፣ የወለዷቸው ልጆች ብዛት ካልወለዱ «0» ይሞላ

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በሕይወት የተወለዱ ወንዶችእና ሴቶች ልጆች ብዛት በንዑስ ዓምድ 37 የሚመዘገቡበት ነው።
ካልወለዱ «0» ይሞላል

ዓምድ 21 :- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከወለዱ ልጆች የሞተ ብዛት

በዓምድ 20 ላይ ልጅ መውለዳቸው የተመዘገበላቸው ሴቶች በዓምድ 21 ላይ ደግሞ ከነዚህ ውስጥ ስንት ልጆች እንደሞተ በንዑስ ዓምድ 38 ይመዘገባል::ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 20 አንድ ወይም ከዚያ በላይ ለተሞላላቸው ብቻ መሆኑን መስተዋል አለበት::